የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፲፱
አዲስ አበባ ጥር ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 19
ADDIS ABABA, 6th February, 2025

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፶፰/፪ሺ፲፯

የኤሌክትሮኒክ ፊርማ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ..........................................ገጽ ፲፯ሺ፮፻፶፱

## Content

Proclamation No. 1358/2024

Proclamation to provide for the Amendment of the Electronic Signature Proclamation……Page 17659

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፶፰/፪ሺ፲፯

## የኤሌክትሮኒክ ፊርማ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኤሌክትሮኒክ ፊርማ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፪/፪ሺ፲ አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ደንብ መመሪያዎችን አውጥቶ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ውክልና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኤሌክትሮኒክ ፊርማ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፶፰/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION No. 1358/2024

## PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF THE ELECTRONIC SIGNATURE PROCLAMATION

**WHEREAS,** it is necessary to amend the existing Electronic Signature Proclamation No.1072/2018 in order to give the council of Ministers and the Information Network Security Administration the power to issue Regulations and Directives required to implement the Proclamation;

**NOW, THEREFORE**, in according to Article 55 Sub-Article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, the following is declared.

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Electronic Signature Proclamation Amendment Proclamation No. 1358/2024".

**፪. <u>ማሻሻያ</u>**

የኤሌክትሮኒክ ፊርማ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፪/፪ሺ፲ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ ከአዋጁ አንቀጽ ፶፪ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፶፫ ተጨምሮ፣ ነባሮቹ አንቀጽ ፶፫ እና አንቀጽ ፶፬ እንደቅደም ተከተላቸው አንቀጽ ፶፬ እና ፶፭ ሆነው ተሸጋሽገዋል።

" ፶፫. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፪/ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ይህን አዋጅ፣ አዋጁን ተከተሎ የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልግ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።"

**፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀ ሥላሴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**2. <u>Amendment</u>**

Electronic Signature Proclamation No.1072/2018 is here by amended as follows፡

1/ The following new article 53 is added after Article 52 of the Proclamation and the existing Article 53 and 54 are renumbered as Article 54 and 55 respectively.

"**53. <u>Power to issue Regulation and Directive</u>**

1/ The Council of Ministers may issue Regulation necessary for the implementation of this Directive.

2/ Information Network Security Administration may issue Directive Necessary to implement This Proclamation and Regulation to be issued for the implementation of this Proclamation."

**3. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 6th Day of February, 2025**

**TAYE ATSKE- SELASSIE**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**